# ለጋሞ ዞን አስተዳዳሪ ማስጠንቀቂ እንደተጻፈላቸው ታወቀ

በደቡብ ኢትዮጵያ በጋሞ ዞን በአርባ ምንጭ ከተማ እንዲሁም በከተማው ዙሪያ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሐይማኖት ምዕመናንና በሥርዓተ-አገዛዙ አባላት መካከል ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየተካረረ በመጣው አለመግባባት ሳቢያ የሰው ደም በከንቱ እንዳይፈስ ከፍተኛ ጥንቃቄ እንዲያደርግ “የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን” ለጋሞ ዞን ዋና አስተዳዳሪ ማስጠንቀቂያ እንደጻፈላቸው ታወቀ።

ይህ ሊታወቅ የቻለው በቁጥር ሰመኮ/145/2000 ሐምሌ 25 ቀን 2000 ዓ.ም የተጻፈውና በዶክተር ከማ ገብረ ሕይወት “የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን” ዋና ኮሚሽነር የተፈረመው ደብዳቤ ተባዝቶ በአርባ ምንጭ ነዋሪዎች እጅ ከገባ ወዲህ ነው።

በተፈጠረው አለመግባባት ከሃያ በላይ ንጹሐን ዜጎች ተይዘው ለመታሠራቸው ጥቆማ ለኮሚሽኑ የደረሰው መሆኑን የገለፀው ይህ ደብዳቤ በመቀጠል ደግሞ በንፁሐን ሕይወትና ንብረት ላይ አደጋ ደርሶ ከተገኘ አግባብነት ባላቸው ሕጎች በወንጀል፤ በፍትሐ ብሔርና በዲሲፒሊን ሊያስጠይቅ እንደሚችል አስገንዝቧል።

ይህ ደብዳቤ በቀጥታ በደቡብ ኢትዮጵያ ለጋሞ ዞን ፖሊስ መምሪያም የተመዘገበ ሲሆን ለኮሎኔል ወርቅነህ ገበየሁ ለፌደራላዊት ኢትዮጵያ ፖሊስ ኮሚሽን ዋና ኮሚሽነር እንዲሁም ለደቡብ ክልል ርዕሰ መስተዳደር ጽ/ቤት በግልባጭ መላኩ ታውቋል።

EthioLion.com